# ኮቪድ-19 ክትባቶችን የተመለከቱ እውነታዎችን ያግኙ



## ኮቪድ-19 ይበልጥ ተላላፊ እየሆነ ነው

እንደ ዴልታ ያሉት አዳዲስ ልውጥ ዝርያዎች ይበልጥ ተላላፊ፣ ሁለት ጊዜ ወይም ከዛ በላይ በቀላሉ ይሰራጫሉ። ይበልጥ ተላላፊ ማለት ጤነኛ በሆኑ ሰዎችና ለክትባቱ ባልደረሱ ልጆች ላይ እንኳን ሳይቀር በሆስፒታል ተኝቶ መታከምን የሚጠይቁ ኬዞችን ጨምሮ፣ የበለጠ ብዙ ድምር ኬዞች ማለት ነው። ይበልጥ አደገኛ የሆኑ ሚውቴሽን የመጠቃት ዕድልም በጣም ከፍተኛ ይሆናል።

ክትባት ከከባድ በሽታ የሚጠብቅዎት ከመሆኑም በላይ ቫይረሱ በሰውነትዎ ውስጥ በመለወጥ "ቀጣዩ ዴልታ" የሚሆንበትን አጋጣሚ ዝቅ በማድረግ ሁላችንንም ይጠብቃል።



## ክትባቶቹ አስተማማኝ ናቸው

የመጀመሪያው የተፈቀደ የ mRNA ክትባት አሁን ሙሉ በሙሉ በ FDA ጸድቋል፣ እና ሁሉም ክትባቶች የድንገተኛ ጊዜ አጠቃቀም ፈቃድ አላቸው። ሁሉም በስፋት የተሞከሩ ሲሆን በአሜሪካ ውስጥ ካሉ ከ 70% በላይ አዋቂዎች ቢያንስ አንድ መጠን ያለምንም ችግር ተቀብለዋል።

አንድ አዲስ መድኃኒት ሙሉ በሙሉ ፈቃድ እንዲያገኝ FDA ሰፋ ያለ የደህንነትና ውጤታማነት መረጃ ማግኘት፣ የማምረቻ ቦታዎችን መመርመርና ሁሉንም የክሊኒካል እና "በገሃዱ ዓለም" አጠቃቀምን መገምገም ይጠይቃል። ከክትባቶቹ መካከል በሕይወት ያለ ቫይረስ የያዘ ባለመኖሩ ኮቪድ-19 ሊያስተላልፉብዎ ወይም ዲ.ኤን.ኤዎን ሊቀይሩ አይችሉም።



## አለመከተብ ማለት ያለውን መልካም እድል አለመጠቀም ማለት ነው

የ COVID-19 ኬዞች እየጨመሩ ሲሄዱ ንግዶች፣ አሰሪዎች እና ዝግጅቶች ክትባትን ይመርጣሉ አልፎ ተርፎም ይፈልጋሉ። ከቤተሰብዎ እንዲርቁ፣ መሥራት እንዳይችሉ፣ በሕይወትዎ ውስጥ ያሉ አጋጣሚዎችን እንዲያጡ፣ አልፎ ተርፎም ሆስፒታል እንዲገቡ ሊያደርግዎ የሚችል የኮቪድ-19 ኢንፌክሽንም ሁልጊዜ አለ።

በሕይወት ውስጥ ያለምንም ችግር የመሳተፍ ነፃነት ማግኘት የመከተብን ያህል ቀላል ነው።

VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH

ALEXANDRIA HEALTH DEPARTMENT · Protecting and Promoting Health

ዛሬዉኑ ከትባት ለመውሰድ ቀጠሮ ይያዙ! የኮቪድ.19 መስመር በ 703-746-4988 ላይ ይደውሉ ወይም alexandriava.gov/Vaccines ን ይጎብኙ።

Updated 9/9/2021



## ክትባቶቹ ከክፍያ ነፃና ለማግኘትም ቀላል ናቸው

በአሁኑ ጊዜ ክትባቱ በአሌክሳንድሪያ እድሜያቸው 12 እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ ይገኛል። በአቅራቢያዎ በሚገኙ በርካታ ቦታዎች፣ ሕዝብ በሚበዛባቸው ቦታዎች በሚቋቋሙ ጊዜያዊ ክሊኒኮች፣ በዶክተሮች ቢሮዎች፣ በፋርማሲዎችና በየመዝናኛ ማዕከላቱ ያለቀጠሮ እና በቀጠሮ በየቀኑ በበርካታ ቦታዎች ክትባቶች ይቀርባሉ!



## ክትባቶቹ የረጅም ጊዜ የጤና ችግሮችን አያመጡም ኮቪድ-19 ግን ሊያመጣ ይችላል

እንደ ልብ ችግር፣ የአተነፋፈስ ችግር፣ አልፎ ተርፎም የአንጎል ጉዳትን ጨምሮ ዘላቂ ሊሆን የሚችሉ በከባድ የኮቪድ-19 ሕመም ምክንያት የሚከሰቱ ተጓዳኝ ውጤቶች አሉ።

እንዲሁም፣ የማያቋርጥ እና/ወይም እንደገና የሚከሰቱ ምልክቶች (አንዳንድ ጊዜ ረጅም ኮቪድ ይባላል) የማንኛውም የኮቪድ-19 ሕመም፣ መለስተኛም ቢሆን ውጤት ሊሆን ይችላል። እነዚህ የረጅም የኮቪድ ምልክቶች በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ጣዕም/ሽታ መለየት ካለመቻል እስከ ለወራት የሚቆይ ድካም የሚደርሱ ሊሆኑ ይችላሉ፣ እንዲሁም አንዳንድ ምልክቶች ፈጽሞ ላይጠፉ ይችላሉ።



## ክትባቶቹ የበለጠ ይጠብቁዎታል

ኮቪድ-19 ይዞኝ ሊሆን ይችላል ብለው ቢያስቡም እንኳ፣ ሙሉ በሙሉ በመከተብ የተሻለ ጥበቃ ያገኛሉ። በቅርቡ የተደረገ አንድ ጥናት እንዳመለከተው ኮቪድ-19 የተያዙ ያልተከተቡ ሰዎች ሙሉ በሙሉ ክትባት ከተሰጣቸው ሰዎች ጋር ሲነጻጸሩ በኮቪድ-19 በድጋሚ የመያዝ አጋጣሚያቸው ከ2 እጥፍ የሚበልጥ ነው።

ሙሉ ክትባት በኮቪድ-19 እንደገና ከመያዝ የተሻለ ጥበቃ ያስገኛል፣ በተለይ ደግሞ ሁለተኛው ሕመም እንደ ዴልታ ዓይነት የቫይረሱ የተለየ ዝርያ ከሆነ።

VDH VIRGINIA DEPARTMENT OF HEALTH

ALEXANDRIA HEALTH DEPARTMENT — Protecting and Promoting Health

ዛሬዉኑ ከትባት ለመውሰድ ቀጠሮ ይያዙ! የኮቪድ.19 መስመር በ 703-746-4988 ላይ ይደውሉ ወይም alexandriava.gov/Vaccines ን ይጎብኙ።